**የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ**
**መጋቢት 06 ቀን 2016 ዓ.ም. የደረሰውን የሲስተም ችግር ተከትሎ የተፈጠረውን የአገልግሎት ማቋረጥ በተመለከተ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ**
**መጋቢት 9 ቀን 2016 ዓ.ም. ከቀኑ 9:30**
**የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋናው መስሪያ ቤት የፕሬዚደንት መሰብሰቢያ አዳራሽ**
**አዲስ አበባ**

እንደሚታወቀው ባንካችን እ.ኤ.አ. ከ2022 ጀምሮ ሁሉን አቀፍ የሆነ ትራንስፎርሜሽን ትግበራ ውስጥ ሲሆን ዓለም-አቀፍ ደረጃውን የጠበቀና የኢትዮጵያን መፃዒ ጊዜ በፋይናንስ የሚመራ ባንክ ለመሆን ርዕይ አንግቦ ከ140 በላይ ኢኒሼቲቮ ቀርፆ እየሰራ ይገኛል። በመሆኑም ይህን ዓለም-አቀፍ ባንክ የሚያስብለውን ለፋይናንስ ስጋት ትኩርት የሚሰጥ፣ ደንበኛ ተኮር፣ በዲጂታል ግንባር ቀደም እና ወጪ ቆጣቢ አሰራር ለማስፈን እና የደንበኞችን እርካታ ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር የዲጂታል ባንክ አገልግሎቶች ላይ ባንካችን በየጊዜው ማሻሻያዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል። ለዚህም ከቅርብ ወራት በፊት የሞባይል ባንክ እና የሞባይል ዋሌት መተግበሪያዎች ላይ ያደረግናቸው ለውጦች ማሳያዎች ሲሆኑ ለደንበኞች በግልፅ የማይታዩ ነገር ግን የአገልግሎት አሰጣጥን የሚያቀላጥፉ፣ አዳዲስ አገልግሎቶችን የሚጨምሩ፣ የፋይናንስ እንቅስቃሴ ደህንነትን የሚያጠናክሩ፣ የቴክኖሎጂ ማሳደጊያ ስራዎችን እንዲሁም ሌሎች ለውጦችን በቋሚነት እያከናወነ ይገኛል። ይህ የለውጥ እንቅስቃሴ በሃገር ውስጥ ገበያ ታዋቂ የሆንበትን የዲጂታል አሰራር ለማዘመን አስፈላጊ በመሆኑ ባንኩ ከመቼውም ጊዜ በላይ አጠናክሮ የሚቀጥልበት ይሆናል።

በበጀት ዓመቱ የስምንት ወር የባንክ እንቅስቃሴ የዲጂታል አገልግሎት ተጠቃሚ ደንበኞች ቁጥር 32 ሚሊዮን ያለፈ ሲሆን ጠቅላላ የተፈፀመ የሒሳብ ዝውውር መጠን ደግሞ በቁጥር 800 ሚሊዮን እና በገንዘብ መጠን ደግሞ ብር 10 ትሪሊዮን ነው። ይህ የዲጂታል የሒሳብ እንቅስቃሴ ባንኩ ካከናወነው ጠቅላላ እንቅስቃሴ 73 በመቶ የሚሸፍን ሲሆን በቀን ውስጥ ከ4 ሚሊዮን የሚበልጡ ደንበኞችን ያስተናግዳል። በየአመቱ የዲጂታል የገንዘብ ዝውውር ቁጥር እየጨመረ የመጣ ሲሆን አምና ከነበረበት ተመሳሳይ ወቅት አንፃር በዚህ ዓመት የ150 ሚሊዮን (16%) ለውጥ አሳይቷል።

በአሁኑ ጊዜ በሃገሪቱ የትኛውም አቅጣጫ የሚገኙ ሁሉም ቅርንጫፎች በኮር ባንኪንግ ቴክኖሎጂ የተሳሰሩ በመሆናቸው እና የዲጂታል አማራጮቹም ከዚሁ ሲስተም ጋር በቅንጅት የሚሰሩ ስለሆኑ አገልግሎቶቻችን በሙሉ ያለምንም ችግር በየትኛውም ጊዜ እና ቦታ ለደንበኞች ተደራሽ እንዲሆኑ ደህንነቱ የተጠበቀ አሰራር መኖሩ ግድ እንደሆነ ያምናል። ለዚህም ከመረጃ መረብ ጥቃት የፀዱ እንዲሆኑ ባንካችን በትጋት በቀን 24 ሰዓት በሳምንት 7 ቀን ያለማቋረጥ በመስራት ላይ ሲሆን የመረጃ መረብ ጥቃት እንዳይከሰት የመከላከል ስራ፣ የሚገኙ የጥቃት አይነቶችን በየፈርጁ በመለየት የምርምር፣ ትንተና እና ትንበያ ስራ በመስራት በባንኩ ኢ-ሜይል እና በቀጥታ የባንኩ የተለያዩ ሲሰተሞች ላይ የሚካሄዱ የሳይበር ጥቃቶችን በመለየት ከመረጃ መረብ ደህንነት አስተዳደር እና

ከኢ.ትዮ ቴሌኮም ጋር በመተባበር እርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል። እ.ኤ.አ. በ2022/23 በጀት ዓመት ብቻ በአጠቃላይ ባንኩ ከ18,000 በላይ በ2023/24 በጀት ዓመት ደግሞ ከ9,913 በላይ የደህንነት ጥቃት ሙከራዎችን ያከሸፈ ሲሆን ባለፉት ስምንት ወራት ከባንኩ የግንኙነት መረብ ውጪ ከተላኩ 1,061,910 ኢ-ሜይል ውስጥ 527,067 (ወደ 50% ገደማ) የሚሆኑት ደግሞ ያልፀዱ በመሆናቸው አስፈላጊው እርምጃ ተወስዶባቸዋል።

ባንኩ የመረጃ ደህንነቱን ለማጠናከር የመረጃ መረብ ደህንነት አስተዳደር የሚያወጣቸውን መመሪያዎች እንዲሁም ዓለም-አቀፍ ስታንዳርዶችን በመተግበር የPCI DSS (Payment Card Industry Data Security Standard) ሰርቲፊኬት የተቀበለ ሲሆን በመጪው አንድ ወር ውስጥም የISO 27001 የመረጃ ደህንነት ስታንዳርድ ትግበራ ማረጋገጫ ለማግኘት ዝግጅቱን አጠናቋል። በአሁኑ ጊዜ የባንኩ የመረጃ ደህንነት ስራ አመራር እጅግ ዘመናዊ፣ በስርዓት የሚመራ እና በቴክኖሎጂ እና በብቁ ባለሞያዎች የተደገፈ በመሆኑ በሃገራችን ላሉ ለሁሉም የፋይናንስ እና ሌሎች ተቋማት እንደ ማሳያ የሚሆን ቁመና ያለው ነው።

ይህም ሆኖ በዚህ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ዘመን ማንም ተቋም ቴክኖሎጂ ከሚያመጣቸው የውስጥም ሆነ የውጭ አደጋዎች ፈፅሞ የተጠበቀ ሊሆን አይችልም፡፡ ይነስም ይብዛም የተለያዩ ችግሮች ሊገጥሙት ይችላሉ፡፡ ባንካችን ከዚህ የተለየ አይደለም በተለያየ ፖለቲካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ምክንያት ሀገራችንን ማጥቃት ሲፈለግ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ግንባር ቀደም ኢላማ (Target) ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በየቀኑ ከተለያዩ አለም አቀፍ አካባቢዎች በየቀኑ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ጥቃቶች ሲሞከርበት ቆይተዋል፡፡ ነገር ግን ጠንካራ የሳይበር ጥቃት መከላከያ ቴክኖሎጂ እና የሰለጠነ ባለሙያ ስላለን እነዚህን የውጭ ጥቃቶች ተቋቁመን ዘልቀናል፡፡

ነገር ግን ባለፈው አርብ መጋቢት 06 ቀን 2016 ዓ.ም ሌሊት አንድ የውስጥ ችግር አጋጥሞናል፡፡ ይኸም ችግር ለተለያዩ ሌቦች ላልተገባ ተግባር አጋልጦናል፡፡ይኸም እጅግ በጣም ያስደነገጠንና ያሳዘነንም ነገር ነው፡፡

ችግሩ የተከሰተውም አንድ የሂሳብ ማስታረቅ ቅልጥፍና እንዲያመጣ ታስቦ የተሰራ የሲስተም ማሻሻያ ሲተገበር ስሕተት በመፈጠሩ ለሌቦች ቀዳዳ መክፈቱ ነው፡፡ አሁንም የኦዲት ስራው ስላልተጠናቀቀ ዝርዝር ጉዳይ ለማቅረብ አልቻልንም፡፡ ሆኖም በተለያየ ሚዲያ ያልተገባ ወሬ እየተናፈሰ ስላለ ለሕዝባችን ያለንበትን ሁኔታ ማሳወቅ ስላለብን ይህ መግለጫ እንዲዘጋጅ ሆኗል፡፡

አጭር የሂደቱ ዘገባ

1. የሲስተም ማሻሻያው የተተገበረው አርብ መጋቢት 06 ቀን 2016 ዓ.ም ከምሽቱ 3 ሰዓት አካባቢ ነበር፤
2. ከሌሊቱ ወደ ስምንት ሰዓት አካባቢ ችግር እንዳለ እና ያልተገባ የግብይት ሂደት መኖሩን በዲስትሪክት በኩል ለባንካችን IT ጥቆማ ደረሰ፤
3. የIT ኃላፊዎች ተጠራርተው ሌሊቱን ወደ ቢሮ በመምጣት አንዳንድ የተጠረጠሩ አገልግሎቶች እንዲቋረጡ ተደርጓል፤
4. ይኸም ሆኖ ችግሩ ሙሉ በሙሉ እንዳልቆመ ስለታወቀ ወደ 11፡30 አካባቢ ሁሉም የዲጂታል አገልግሎቶች እንዲቆሙ ተደረገ፤
5. ቅዳሜ መጋቢት 07 ቀን 2016 ዓ.ም ጠዋት የቅርንጫፍ አገልግሎቶችም እንዲቆሙ ተደረገ፤
6. ከዚያ ሌሊቱን ወደ ግል ባንኮች እና ወደ ቴሌ ብር የተላለፉት ግብይቶች ተለቅመው ወጥተዋል ለየተቋማቱ እንዲያቆሙልን የትብብር ጥያቄዎች ተልከዋል፤
7. ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት እንደ ብሔራዊ ባንክ፣ ኢትስዊች እና የፀጥታ አካላት እንዲያውቁት ተደርጓል፤
8. አገልግሎቶቻችን በሲስተም ችግር ምክንያት እንደተቋረጠ ለደንበኞቻችን በማሳወቅ እና ይቅርታ በመጠየቅ በትዕግስት እንዲጠባበቁን መልዕክት በተከታታይ አስተላልፈናል፤
9. ሌሊቱን በሙሉ ግብይት ሲፈፀምባቸው የነበረት ሂሳቦች በሙሉ እስኪጣራ ድረስ ለጊዜው እንዲታገድ (Block እንደሆኑ) ተደርጓል፤ ይኸም ኪሳራ ለመቀነስ የተወሰደ እርምጃ ነው፤
10. ቀጥሎም አዲስ የተተገበሩት የሲስተም ማሻሻያዎች እንዲቀለበሱ ተደርጓል፤
11. ቅዳሜ ከቀኑ 7 ሰዓት ጀምሮ የቅርንጫፍ አገልግሎቶች፣ የATM አገልግሎት፣ የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎቶች፣ የCBE Birr አገልግሎት እና የኢንተርኔት አገልግሎት በተከታታይ በተራ ስራ እንዲጀምሩ ተደርጓል፡፡
12. አገልግሎቱም እስከ ምሽቱ 2 ሰዓት ድረስ እንዲቀጥል ማድረጋችንን አሳውቀን ደንበኞች በተረጋጋ ሁኔታ እንዲስተናገዱ አድርገናል፤
13. በቀጣይ ከፍተኛ ያልተገባ ግብይት የፈፀሙ አካላትን እየለየን ለሕግ አካላት ማቅረብ ጀምረናል፤
14. እጅግ በጣም ያሳዘነን ደግሞ ነገ የሀገር ተረካቢ ይሆናሉ ብለን የምንጠብቃቸው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በወንጀሉ ዋና ተዋናይ ሆነው ማየታችን ነው፡፡ በየአካባቢው ያሉ የዲስትሪክት ኃላፊዎች በየአካባቢው ከሚገኝ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመቀናጀት የወሰዱትን ገንዘብ እንዲመልሱ እየተደረገ ይገኛል፤

15. በዕለቱ ግብይት ከፈፀሙ ደንበኞች ውስጥ የራሳቸውን ገንዘብ ያንቀሳቀሱና የሌላቸውን ገንዘብ ወደተለያዩ ሂሳቦች እና ተቋማት ያስተላለፉትን የመለየት ስራ ቀጥሏል፤
16. ትርፍ ገንዘብ የወሰዱትም እንዲመልሱ ወይም በሕግ እንዲጠየቁ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፤
17. የችግሩ መሰረታዊ መንስኤ እና ያስከተለው ጉዳትም ምርመራ ሲጠናቀቅ ዝርዝር መረጃውን የምናሳውቅ ይሆናል፤
18. በዚህ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ድጋፍ ያደረጉልን አካላት በተለይም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ የኢትዮ ቴሌኮም፣ የኢትዮጵያ ባንኮች ማህበር፣ የፌዴራልና የክልል ፖሊስ፣ የዩኒቨርሲቲዎች አስተዳደር፣ የኢትዮጵያ ፋይናንሻል ኢንተለጀንስ፣ INSA፣ ኢትስዊች፣ የግል ባንኮች፣ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት፣ የተለያዩ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ተቋማት እና የረዱንን ሁሉ እጅግ በጣም እናመሰግናለን፡፡

በቀጣይ በደረሰው ጉዳት ላይ ዝርዝር ምርመራ ማጠናቀቅ ጉዳት አድራሾች የወሰዱትን ገንዘብ በፈቃደኝነት እንዲመልሱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤ ይኸም ካልተሳካ አፋጣኝ የሕግ እርምጃ መውሰድ በትኩረት የምንሰራው ተግባር ነው፡፡ በዚህ ጉዳዩ ላይ የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ የጀመሩትን ድጋፍ አጠናክረው እንዲቀጥሉልን በዚህ አጋጣሚ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡ የሲሲተም ማሻሻያዎችንም ትኩረት በመስጠት እና ጥንቃቄ ተጨምሮበት የሚቀጥል መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

በዚህ አጋጣሚ በባንካችን ላይ የደረሰው ጉዳት ከባንካችን አቅምና ኃብት አንፃር እጅግ በጣም አነስተኛ ሊባል የሚችል በመሆኑ በባንካችን ላይ የሚያደርሰው የጎላ ተፅእኖ የለም፡፡ ከሁሉም በላይ የባንካችን ደምበኞች ሂሳብ ጋር ምንም ግንኙነት ስለሌለው ደንበኞቻችን ኃሳብ እንዳይገባችሁ እያልን የተለመደው ደንበኝነታችሁ ሁሌም ከሚተማመኑበት ባንካችሁ ጋር ይሁን እንላለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ